# የ Boston Public Schools የብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪ ፕሮግራም ማሻሻያ ለELL ግብረ ኃይል

ማርች 30/2023

# አጀንዳ

- የብዝሃ ቋንቋ ተማሪ ፕሮግራም መግለጫ
- የአካታችነት ትግበራ
- የትምህርት ቤት እቅድ ለባለ ሁለት ቋንቋ ፕሮግራም ማስፋፊያ

# የብዝሃ ቋንቋ ተማሪ ፕሮግራሚንግ

# አሁን ላይ በ BPS ውስጥ ያሉ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች ፕሮግራም አማራጮች

1. የሸሩን የእንግሊዝኛ መመሪያ፡ ቋንቋን መሰረት ያደረገና ብዝሃ ቋንቋ
2. ባለ ሁለት ቋንቋ
3. ውስን የሆነ ወይም ተቋርጦ የነበረ መደበኛ ትምህርት (SLIFE) ላላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ የቋንቋ ስልጠና (HILT)
4. ESL በከፍተኛ ሁኔታ የተለየ ልዩ ትምህርት ፕሮግራም
5. ESL በአጠቃላይ ትምህርት

# የሽፋን የእንግሊዝኛ መመሪያ (BPS SEI) [ELD 1-3]

## ቋንቋን መሰረት ያደረ

- የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት ELD 1-3 ላሉ ML ዋና የትምህርት ይዘት መመሪያን የበለጠ ለመገንዘብ የሚያስችሉ ስልቶች ጋር ተካቶ ይቀርባል።
- ትምህርቱ የሚሰጠው በእንግሊዘኛ ሲሆን እንዲሁም ደጎም ለተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ድጋፍ ይሰጣል።
- በዚህ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ተመሳሳይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚናገሩ ሲሆን ያሉበት የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት (ELD) ከ 1 እስከ 3 ደረጃ ላይ ይገኛል።
- የሽፋን ትምህርት በክፍል ደረጃ ትምህርታዊ ይዘት ቦታዎችን ለ ML ተማሪዎች አስበልጦ ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ ተብሎ ያለመ ነው።
- BPS በስፓኒሽ፣ በሄይቲ ክሪኦል፣ በኬፕ ቨርዴያን ክሪኦል፣ በቬትናምኛና በቻይንኛ የ SEI ፕሮግራሞች አሉት።

## ብዝሃ ቋንቋ

- ELD 1-3 ለሆኑ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በአምስቱ BPS ቋንቋን መሰረት ያደረጉ SEI ፕሮግራሞች ውስጥ አንድ ያልሆ ለ ML ተማሪዎች ይገኛል።
- የአካዳሚክ ይዘት መመሪያን ELD 1-3 ላሉ ML ተማሪዎች የበለጠ ለመረዳት የሚያስችሉ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ስልቶችን ያካትታል።
- በዚህ ፕሮግራም መመሪያ የሚሰጠው በእንግሊዘኛ ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ከሆነ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ድጋፍ የሚገኝ ከሆነ ይህ ለተማሪዎች ይሰጣል።

# የሁለት ቋንቋ ና የውርስ ቋንቋ ትምህርት [ELD 1-5, FEL]

- LOOK Act (2018) በመተግበር ላይ BPS እንደ ባለሁለት-መንገድ ጠላቂ ፕሮግራሞች፣ የውርስ ቋንቋ ፕሮግራሞችን የመሳሰሉ ተጨማሪ የሁለት ቋንቋ እድሎችን እንዲጨመሩ ለማድረግ ይፈልጋል።
- ፕሮግራሞች በአሁኑ ጊዜ በስፓኒሽ፣ በሄይቲ ክሪኦል፣ በ ASL፣ በቬትናምኛና በኬፕ ቨርዴያን ክሪኦል የሚሰጡ ይሆናል።
- የትምህርት ክፍሉ ባለ አፍ መፍቻ ቋንቋና እንግሊዘኛን በበላይነት የሚናገሩ ተማሪዎችን ያካተተ ነው።
- ሁሉም ተማሪዎች ሁለቱንም ቋንቋዎች ማንበብ፣ መጻፍ፣ መናገርና መረዳት የሚማሩ ሲሆን ይህም በመሰረታዊ የትምህርት ይዘት መመሪያ ወይም ግልጽ የቋንቋ ትምህርትን በሁለቱ ቋንቋዎች ብቁ በሆኑ መምህራን ይማራሉ።
- የሁለት ቋንቋ መርሃ ግብሮች አላማው ለሁለት ቋንቋ ተናጋሪና ሁለት ቋንቋን ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ተማሪዎች የታለመ ነው።

HILT ለ SLIFE
[HILT 1-2/ELD

# ውስን የሆነ ወይም ተቋርጦ የነበረ መደበኛ ትምህርት (SLIFE) ላላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ የቋንቋ ስልጠና (HILT)

BPS ይህን ፕሮግራም እድሜያቸው 8 ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ አዲስ ለመጡ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ትንሽ ወይም ምንም ለሆነ፣ ወይም መደበኛ ትምህርታቸው በትውልድ አገራቸው ለተገደበ ወይም ለተቋረጠ ተማሪዎች ይመክራል።

በ HILT ፕሮግራሞች፣ ተማሪዎች የሚከተሉትን ያገኛሉ፡

- ጠንካራ ትምህርታዊ የንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሁም ማንበብና መጻፍ እድገት
- ማንበብ፣ መጻፍ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስና ታሪክ/ማህበራዊ ጥናቶች በሚኖሩ ጊዜ እንዲማሩ ለመርዳት የተነደፈ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት
- እንደ ቴክኖሎጂ፣ ጥበባትና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ያሉ ተጨማሪ ክፍሎች።

# ESL በከፍተኛ ሁኔታ የተለየ ልዩ ትምህርት ፕሮግራም [ELD 1-5, FEL]

- የአካል ጉዳት ያለባቸው የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች የ ESL አገልግሎቶችን የሚያገኙት እራሱን በቻለ የልዩ ትምህርት ክፍል ውስጥ ሲሆን በልዩ የትምህርት እቅዳቸው (IEP) መሰረትም ልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ይሆናል።
- መመሪያው የሚሰጠው በእንግሊዘኛ ሲሆን ከተገኘም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ድጋፍ ይሰጣል።
- ተማሪዎች EL ከክፍል ደረጃ ይዘት ጋር ትርጉም ባለው መልኩ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ስነምግባር-ተኮር ትምህርታዊ ቋንቋን እንዲያዳብሩ ከ SEI ከተፈቀደላቸው፣ የይዘት ፈቃድ ካላቸው መምህራን የሽፋን የይዘት ትምህርት ያገኛሉ።
- በተማሪው ባለው የአካል ኡዳት ሁኔታ ላይ መሰረት በማድረግ በ ESL አገልግሎቶች ላይ በ IEP ውስጥ እንደተገለጹት ለውጦች ሊደረጉ ይችላሉ።

# ESL በአጠቃላይ ትምህርት (ከሽፋን መመሪያ ጋር) [ELD 1-5]

- ማንኛውም ELD 1-5 ያለበትና መደበኛ SEI ፕሮግራም ሳይኖረው በትምህርት ቤት የተመደበ ተማሪ የተብራራ የ ESL ትምህርት የሚያገኝ ይሆናል
- ELD 4-5 ላሉ አንዳንድ ተማሪዎች፣ በእንግሊዘኛ/በመጻፍና ማንበብ ኮርስ አንድ ላይ በማድረግ ESL ማግኘት ይችላሉ
- በአጠቃላይ ትምህርት ክፍል ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ELD 1-5 EL በክፍል ደረጃ ይዘት ትርጉም ባለው መልኩ መሳተፍ እንዲችሉና በስነምግባር ላይ የተመሰረተ የትምህርት ቋንቋ እንዲያዳብሩ በ SEI ተቀባይነት ባለው መምህር የሽፋን የይዘት ትምህርት ያገኛሉ
- ትምህርቱ የሚሰጥበት ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው
- በዚህ ምደባ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ብቃት ካላቸው አቻዎቻቸው ጋር አብረው የሚማሩበት ተደባልቀው የሚማሩበት ክፍል ውስጥ ሆነው ነው
- በአጠቃላይ ትምህርት ወይም በልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ሁሉም ተማሪዎች ELD 1-5 ከ SEI ተቀባይነት ባለው መምህር የይዘት መመሪያን ያገኛሉ

| የፕሮግራም አይነት | ቋንቋ እንዲሁም ማንበብና መጻፍ | የይዘት አካባቢ የትምህርት ቋንቋ(ዎች) | ምዝገባ | የመምህራን ብቃት* |
|---|---|---|---|---|
| **SLIFE** | የቤት ቋንቋና ESL | የቤት ቋንቋና እንግሊዝኛ | ብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች SLIFE ተብለው ተለይተዋል | የክፍል ደረጃና የይዘት ፈቃድ፣ ESL |
| **SEI** | ESL | እንግሊዘኛ ከቤት ቋንቋ ድጋፍ ጋር | ብዝሃ ተማሪዎች ደረጃ 1 - 3 | የክፍል ደረጃና የይዘት ፈቃድ፣ ESL |
| **የውርስ ቋንቋ** | የቤት ቋንቋ | የቤት ቋንቋ | ብዝሃ ተማሪዎችና የቀድሞ ML | የአለም ቋንቋ ፈቃድ በልዩ ቋንቋ K-6 ወይም 5 -12። MTEL በእንግሊዝኛ ማንበብና መጻፍ። |
| **ሁለት ቋንቋ** | የቤት ቋንቋና እንግሊዝኛ | የቤት ቋንቋና እንግሊዝኛ | የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች፣ የቀድሞ ML፣ እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋነቋቸው የሆኑ | የክፍል ደረጃ እና የይዘት ፈቃድ; ESL; የሁለት ቋንቋ ድጋፍ |
| **ESL በአጠቃላይ ትምህርት/ ልዩ ትምህርት** | ESL | እንግሊዘኛ | የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች ደረጃ 4 - 5 | ESL |



* ሁሉም አስተማሪዎች በ SEI ተቀባይነት ያላቸው - የ MA መምህራን ፈቃድ መስፈርቶች ናቸው

# በBPS ውስጥ ያሉ የአሁን ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ፕሮግራሞች

## ባለሁለት ቋንቋ ( TWI)

ስፓኒሽ/እንግሊዘኛ
- Umana (K1-8)
- Greenwood (K1-8)
- Hernández (K1-8)
- Hurley K-8 (K1-8)
- Muñiz (9-12)

ASL/እንግሊዝኛ
- Horace Mann School መስማት ለተሳናቸውና መስማት አስቸጋሪ ለሆነባቸው ትምህርት ቤት (K-12)

የሄይቲ ክሪኦል/እንግሊዘ
- Mattahunt(ከ1-4ኛ ክፍል)

ቬትናምኛ/እንግሊዘኛ
- Mather (ከ1-2ኛ ክፍል)

## ሌላ የ NL መመሪ
- በ ቡርኬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ Cabo Verdean ቋንቋና ባህል ኮርስ

## SLIFE

ስፓኒሽ
- Curley
- Umana
- Hennigan K-8
- Mildred Ave
- Blackstone
- BCLA/ McCormack
- Charlestown High
- Newcomers Academy
- Frederick Pilot
- East Boston High School

ሓይቲያን ክሬኦሌ
- Taylor
- Tech Boston
- Newcomers Academy

ካቦ ቬርደን ክሪኦል
- Orchard Gardens
- Dearborn STEM
- Newcomers Academy

ብዝሃ ቋንቋ
- Newcomers Academy
- Brighton High School
- Edison K-8
- Taylor
- Frederick
- Madison Park Technical Vocational

# አካታችነ
# ት

# የማካተት አተገባበር

ተከታታይ የሆነ አገልግሎቶችን ለማቅረብ BPS ከ Great City ትምህርት ቤቶች ምክር ቤት የተሰጡ ምክሮችን ተግባራዊ እነዲሆኑ ለማስቻልና የማካተት ትግበራ እቅዳችንን ለመፈጸም የብዙ አመት ሂደቱን እንዲጀመር አድርጓል፡፡

ይህ ትኩረቱ የሚያካትተው፡

1. ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አካታች ትምህርትን ለመደገፍ እንዲቻል የተለየ የሰራተኞች የሙያ ማጎልበቻና የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች የቤት ቋንቋ ድጋፍና ትምህርት ማግኘት
2. ለደረጃ 2 እና ለደረጃ 3 ጣልቃገብነቶች መገልገያዎችን ጨምሮ ለ MTSS መሰረታዊ ነገርን ማሻሻል
3. ለመምህራን በልዩ ሁኔታ የተነደፈ ትምህርት እንዲሰጡ ለማስቻል ስልጠና መስጠትና ግብዓቶችን ማቅረብ
4. ዳታን በመጠቀም ሰራተኞቹ አካል ጉዳተኛ ሊሆኑ የሚችሉ እንዲሁም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ወይም የ 504 ዝግጅቶች እቅድን የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎችን ጨምሮ ተማሪዎችን በሚገባ መለየት ይችላሉ
5. የ IEPዎችን ጥራት ማሻሻል



# ለ MLWD አካታችነት

- አካል ጉዳተኛ የሆኑ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች (MLWD) በሁለቱም OMME እና በልዩ ትምህርት ድጋፍና ቁጥጥር በትምህርት ቤቶች ያገለግላሉ።
- MLWD የልዩ ትምህርት ፍላጎቶች ከ IEP ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ የሚሟሉ ይሆናል።
- የ MLWD የቋንቋ እድገት ፍላጎቶች በ ELD ደረጃ፣ የቤት ቋንቋ እና/ወይም የወላጅ ሞግዚት የሁለት ቋንቋ ምርጫ በሚወስኑ የፕሮግራም ምደባቸው የሚሟላ ይሆናል። የማካተት እቅድ ቡድኖች እንደ የትምህርት ቤቱ የትምህርት አሰጣጥ አካል የቋንቋ ፍላጎቶችን ቅድሚያ እንዲሰጡ።
- የ MLWD ያለው የይዘት አካባቢ ትምህርት በሁለቱም በልዩ መምህራን እንዲሁም በ ESL ፍቃድ በተሰጣቸው/በእውቅና በተሰጣቸው መምህራን ይደገፋል።
- ለ MLWD “መካተት” በምንጠቅስ ጊዜ SEI፣ ባለ ሁለት ቋንቋ፣ HILT ወይም አጠቃላይ ትምህርታቸውን ከ ESL ምደባ ጋር የምናይበት ነው።
- IEP ተገቢ የሆነ የተለየ ምደባ ከፈለገ፣ ESL እንዲሁም የሽፋን መመሪያ በምደባው ውስጥ ለዚያ MLWD ይቀርባል።

# የማካተት ድጋፎች

**ክልላዊ ሞዴል፡** የልዩ ትምህርት ረዳት ዳይሬክተሮችና የብዝሃ ቋንቋ እኩልነትና ተጠያቂነት ልዩ ባለሙያዎችን ጨምሮ ሁሉንም የትምህርት ቤቶች ፍላጎቶች ድጋፍ ለማድረግ የተነደፉ እያንዳንዳቸው 9 ክልሎች ከ12-15 ትምህርት ቤቶች ቡድኖች ያሏቸው አሏቸው። ስለ ክልላዊ ሞዴል እዚህ ላይ በተጨማሪነት ማንበብ ይችላሉ።

**አፋጣኝ ድጋፎች፡**

- አሰልጣኞች የሚያካትቱት ድጋፎች፡
  - አሰልጣኞች በስርዓተ ትምህርት፣ በትምህርትና በማህበራዊ ስሜታዊ ችሎታዎች ላይ ልዩ የሆነ ሙያ ያላቸው ሲሆን ለተግባራዊነቱም ኃላፊነት ላለባቸው በትምህርት ቤት ለሚገኙ ሰራተኞች ስልጠናዎችንና የስልጠና ክፍለ ጊዜዎችን ያቀርባሉ
  - ለማካተት እቅድ ቡድኖች ስልጠናና ድጋፍ መስጠት
  - ከካንሳስ ዩኒቨርሲቲ የሚገኝ መሳሪያ በመጠቀም የትምህርት ቤት አቀፍ ፍላጎቶች ላይ ግምገማ ማካሄድ
  - አካታች ተግባራትን ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ለትምህርት ቤቶችና መምህራን ግብአቶችንና ድጋፎችን ማቅረብ
  - አካታች ልምምዶች ጨምሮ የብዝሃ ቋንቋና የቤት ቋንቋ ድጋፎችን በማካተት ከOMME ጋር መስራት

- በአፍ መፍቻ ቋንቋን ጨምሮ በ MTSS አስተባባሪዎችና የንባብ ስፔሻሊስቶች፣ ተጨማሪ ሙያዊ እድገትና ከፍተኛ ጥራት ያለው ደረጃ 1 ስርዓተ ትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ
- የሰራተኞችና መተላለፊያ፡ ማካተት፣ ልዩ ትምህርትና የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ልዩ ባለሙያዎች
- የተመደበ ስራ፡ ማካተት እቅድ ማውጣት፣ MLE ፕሮግራምና የትንታኔ ልዩ ባለሙያዎች
- የ IEP ልማት፣ ELD እና MLWD ስልጠና

**እነዚህ ድጋፎች በሙላ ለረጅም ጊዜ ዘላቂነት ያለው ስርአት ለመፍጠር እንዲቻል ለእኛ አስፈላጊ የሆነ መሰረት በመገንባት ላይ ናቸው።**

# የፕሮግራም እቅድ ሂደት

# የትምህርት ቤት ምርጫ ሂደት ለሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞች

BPS የሁለት ቋንቋ ፕሮግራም ማስፋፊያ በጠንካራ እጩነታተው ምክንያት ተለይተው ለታወቁ 10 ትምህርት ቤቶች የ $50,000 የእቅድ አርዳታ ይሰጣል።

- የገንዘብ ድጎማዎችን ለማቀድ የታሰቡ ተግባራት
  - የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ተሳትፎ
  - የፕሮግራም ንድፍ
  - ስርዓተ ትምህርት
  - የመተላለፊያ ትንተና፡ ተማሪዎችና መምህራን

የሚከተሉትን መመዘኛዎች ግምገማ ከተደረገባቸው በኋላ ትምህርት ቤቶቹ ለእቅድ እርዳታው ይመረጣሉ፡

- በወቅታዊ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪ ምዝገባ
- በአካባቢው ባሉ የመጀመሪያ ቋንቋና የተማሪዎች የቤት ቋንቋ
- በትምህርት ቤት ባለ ወቅታዊ ፕሮግራሞች
- በወቅታዊ የሰራተኞች የቋንቋ አቅም
- በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ቁርጠኝነት